# ክፍል ፫

## 3.1 አንቀፅ 39 እና AFD

ይህ አከራካሪ የሆነ አንቀፅ ከመጀመሪያዉም የህገ-መንግሥቱ አካል እንዲሆን የተደረገዉ ከሕወሐት ዓላማ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነዉ። ከዚያም ባሻገር «የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል» የሚለዉን ፅንሰ ሀሳብ ሕወሐት እንደማስፈራሪያም፣ እንደማባበያም፣ እንደማታለያም ይጠቀምበታል። የአንቀጹ በህገ-መንግሥቱ ዉስጥ መኖር የአገር አንድነትን ይፈታተናል የሚሉትን ወገኖች «በመፈቃቀድ ላይ ለተመሠረተ አንድነት መሠረት ነዉ» የሚላቸዉ ሲሆን በአንፃሩ ግን «እኔ ሥልጣን ላይ ከሌለሁ በዚህ አንቀፅ መሠረት ኢትዮጵያ እንዳልነበረች ሆና ትበታተናለችና ኢትዮጵያ እንድትኖር ከፈለጋችሁ ሥልጣኔን በምንም ዓይነት መንገድ አትንኩ» ለማለትም የሚጠቀምበት ይመስላል። የዲሞክራሲን መኖር እንደመስፈርት ለሚያዩት ዕርዳታ ሰጪዎችም «በዛሬዪቷ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የዲሞክራሲ መብታቸዉ ካልተከበረ የራሳቸዉን ዕድል በራሳቸዉ በመወሰን እስከመገንጠል ድረስ የመሄድ መብት አላቸዉ፣ አገራችን የብሔሮችም ሆነ የዲሞክራሲ ጥያቄ በግልፅ የሚነሳባት አገር ስለሆነች ተጨቆንን ለሚሉት ወገኖች ህገ-መንገሥታችን ይህን መብት አረጋግጦላቸዋል» በማለት ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመሆኑ እንደማስረጃ ይጠቀምበታል። በአንቀጹ ላይ በመመሥረትም ሆነ በሕዝባቸዉ ላይ የሚደርሱትን ኢሰብዓዊ በደሎች መሠረት በማድረግ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጠንከር ያለ ጥያቄ የሚያነሱትን ደግሞ የፈለፈላቸዉን ..ጴዶች የጥያቄዉ ታቃዋሚ አድርጎ በማቅረብ «የብሔሮች ጥያቄ የጥቂት ተቃዋሚ ድርጅቶች እንጂ የሕዝቡ አይደለም፣ ሕዝቡ እስከ መገንጠል ድረስ መብት የሰጠዉን ህገ-መንግሥት ከልብ ተቀብሎ የዲሞክራሲን ጣፋጭ ፍሬ እያጣጣመ ነዉ» በማለት ይቀልድባቸዋል። ለአንቀፁ በህገ-መንግሥቱ መካተት ዋናዉ ዓላማ የነበረዉ ግን የታሪክ አጋጣሚና የሁኔታዎች ባልተጠበቀ መንገድ መቀያየር አስቀረዉ እንጂ ሌላ ነበር። ወደዚያ ጉዳይ ከመግባት ግን እንቆጠባለን።

የሚያሳዝነዉ ታዲያ ስንት ጠቃሚ የፖለቲካ ሥራ የሚሠራበት ጊዜ፣ ዕዉቀትና ጉልበት መኖሩም በማይጠቅመዉ አለመኖሩም በማይጎዳዉ በዚህ አንቀፅ ላይ በመከራከር መጥፋቱ ነዉ። አንቀፅ 39 አዉሎ ነፋስ ሆኖ አገር የሚበትን ቢሆን ኖሮ ህገ-መንግሥቱ በፀደቀ በነጋታዉ አገራችን በተበተነች ነበር። የአንቀፅ 39 አለመኖር ለአንድነት ዋስትና ቢሆን ኖሮ እስከዛሬ ሲካሄዱ የነበሩት የነፃነት ትግሎች ሁሉ ባልተካሄዱ ነበር። ኤርትራም የተገነጠለችዉ አንቀጹ የተካተተበት ህገ-መንግሥት ሳይፀድቅ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ደግሞ የሚያሳየዉ አንቀፅ 39 በህገ-መንግሥቱ ዉስጥ ኖረም አልኖረም

ለመገንጠል የፈለገን ሕዝብና ክልል ለማስቀረት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ነዉ:: ስለሆነም በአንቀጽ 39 በህገ መንግሥቱ ዉስጥ መኖር አለመኖር ላይ መከራከር ሳይሆን በእዉነት አስተማማኝ፣ የሚያኮራና የምንመካበት አንድነት ነበረን ወይ? ዛሬስ አንድ ነን? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸዉ በአጥጋቢ ሁኔታ መመለስ ያለባቸዉ:: ይህ አንቀፅ ባይኖርም የዲሞክራሲ መብትና የህዝቦች ነፃነት በተግባር እስካልተረጋገጠ ድረስ የመገንጠል አደጋ ሁሌም አለና:: ስለዚህ አንቀጹን ትተን ተጨባጭ ሁኔታዉን እንይ:: ከምንም በላይ ሕዝቡን እንይ:: ሕዝቡ ምን ያስባል? በአገሩ እየተደረገ ባለዉ ሁሉ ደስተኛ ነዉ? ሌላዉን ጉዳይ ሁሉ ትተን ያለንበት ዘመን የሚጠይቀዉን የመናገር፣ የመፃፍ፣ የማንበብ፣ የፈለገዉን የዜናና የመረጃ ማሰራጫዎች የመከታተል፣ በፈለገዉ ክልል የመኖር፣ የፈለገዉን የመሥራት፣ የመደራጀት፣ የመቃወም፣ ከምንም በላይ ደግሞ ይወክሉኛል ያላቸዉን መሪዎች በነፃነትና በዲሞክራሲያዊ መንገድ መርጦ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቶች ተጎናፅፏል?

ለአገራችን አንድነት የሚያሰጋን የአንቀፅ 39 በህገ-መንግሥቱ ዉስጥ መኖርና አለመኖር አይደለም:: የሚያሰጋን ከአንቀፁ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ስናነሳና ስንጥል በዋና ዋና የፖለቲካ ሥራዎች ላይ ማተኮር አለመቻላችን ነዉ:: ይህ ደግሞ የድርጅት መሪዎችን ጨምሮ ብዙዎች ምንም ትኩረት ያልሰጡት ወይም ሊሰጡት ያልፈለጉት ችግር ይመስለናል:: ፖለቲከኞቻችን በተጨባጭ ሥራዎች ላይ እንደማተኮርና ወደፊት ለመራመድ የሚያስችል ዉጤታማ የሆነ የፖለቲካ ሥራ እንደመሥራት በአንቀፅ 39 ላይ በማነጣጠር እንደማስቲካ ሲያኝኩት ኖሩ:: ማስቲካ እንኳ ለተወሰነ ደቂቃ ታኝኮ ይጣላል፣ አንቀፅ 39 ግን ህገ መንግሥቱ ከፀደቀበት ዕለት ጀምሮ ለዓመታት የሚታኝክ ማስቲካ ሆኖ ኖረ::

የአንቀፁን መኖር የሚቃወሙት የፖለቲካ ድርጅቶች ከቅንጅት አካሄድ ጠቃሚ ትምህርት መቅሰም በቻሉ ነበር:: ቅንጅት አንቀፅ 39 ጥሩ ነዉ አላለም:: በአንፃሩ ደግሞ እንደዛሬዎቹ የAFD ተቃዋሚዎች እዚያ ላይ ተጣብቆ አልነቃነቅምም አላለም:: በህገ-መንግሥቱ ማዕቀፍ ዉስጥ እሠራለሁ፣ በመሆኑም ህገ-መንግሥቱን እቀበላለሁ በማለት ወደ ግንቦት 1997 ምርጫ ሲገባ ተመርጬ ሥልጣን ከያዝኩ ግን በህጋዊ አግባብ የማሻሻያ ሀሳብ (amendment) የማቀርብባቸዉ የህገ መንግሥቱ አንቀጾች ይኖራሉ ከእነዚህም መካከል አንዱ አንቀጽ 39 ነዉ በማለት በግልፅ አስቀመጠ:: የAFD መሥራች ድርጅቶችም ስምምነቱን ሲፈራረሙ በህገ መንግሥቱ ላይ የወሰዱት አቋም ከዚህ የተለየ እንዳልነበር በየስብሰባዉና በልዩ ልዩ መግለጫዎቻቸዉ አብራርተዋል:: በእርግጥ አንቀፅ 39ን የማይቃወሙና ሌሎችን የህገ-መንግሥቱ አንቀጾች የማይቀበሉ የትብብሩ አባል

ድርጅቶች እንዳሉ በተለያዩ መድረኮች አስረድተዋል:: የትብብሩ መስራቾች አጠቃላይ ስምምነት ግን በሚያስማሙን ነጥቦች ላይ አብረን መንቀሳቀስ እንጀምርና ሕወሐትን ጨምሮ በሚካሄደዉ ብሔራዊ ጉባኤ ላይ መሠረታዊ ልዩነቶቻችንን፣ ችግሮቻችንንም ሆነ አለን የምንላቸዉን ጥቄዎች ሁሉ በግልፅነት አቅርበን በምንደርስባቸዉ የመግባባት ነጥቦች ላይ በመመሥረት ወደ ተሻለ እርምጃ እንሄዳለን የሚል መሆኑን ነዉ በተለያየ ወቅት በተለያዩ መድረኮች ላይ የገለፁት:: ታዲያ ይህ አቀራረብ ምን ችግር አለበት? የትስ ላይ ነዉ የአገርን አንድነት የሚጎዳዉ?

አገራችንና ሕዝባችንን በጣም የጎዳዉና ለወደፊቱም የሚጎዳዉ የህገ-መንግሥቱ አንቀፅ 39 ሳይሆን የሕወሐት መሠሪነትና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያለዉ ገደብ የለሽ ጥላቻ ነዉ:: ሕወሐት ደርግን አሸንፎ አዲስ አበባ የገባዉ በብሔር ብሔረሰብ ስም ከጠፈጠፋቸዉ «የተወሰኑ ድርጅቶች» ጋር በመሆን ነበር:: የገዢነቱን ሥልጣን ከተቆጣጠረ በኋላም በግድም በዉድም ተጨማሪ «የብሔረሰብ ድርጅቶችን» በብዛት ፈለፈለ:: ሕዝቡም በግዳጅ ጭምር በሕወሐት ወደተፈለፈሉት የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶች ተገፋ:: የወያኔ መሪዎች ከእነሱ ፍቃድና ቡራኬ ዉጭ የተደራጁትን ሁሉ «ነፍጠኛ» «ትምክህተኛ» «ጠባብ» ብለዉ ፈረጇቸዉ:: ጤናማ የመብት ጥያቄ ያነሱትን ሳይቀር ከእነሱ ዉጭ የተደራጁ በመሆናቸዉ ብቻ የጥቃት ሰለባ አደረጓቸዉ:: ታዲያ ማዉገዝ ያለብን እነዚህንና የመሳሰሉትን የሕወሐት እርምጃዎች ነዉ ወይስ መኖሩም ያልጠቀመዉን አለመኖሩም የማይጎዳዉን አንቀፅ 39?

መታወቅ ያለበት ደግሞ ከAFD መቃወሚያ ነጥቦች አንዱ የሆነዉን አንቀፅ 39ን የሕዝቦቻቸዉን ፍትሃዊ ጥያቄዎች አንግበዉ የሚንቀሳቀሱት ኦነግ ወይም ኦብነግ ህገ-መንግሥቱ ዉስጥ እንዲካተት አላደረጉም:: የአንቀፁ ባለቤት ሕወሐት ነዉ:: የትብብሩ መሥራቾች ያሉት ደግሞ ሕወሐትን ጨምሮ ሌሎችም የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች ሁሉ የሚሳተፉበት ብሔራዊ ጉባኤ ተጠርቶ የችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ በሰላማዊ መንገድ ይፈለግ ነዉ:: የዚህ ዓይነቱ ጉባኤ እንደተባለዉ ከተካሄደ ደግሞ ምናልባትም አዲስ ህገ-መንግሥት ወደመቅረፅ ወይም አሁን ያለዉን ህገ-መንግሥት ወደማሻሻል የሚያመራ የጋራ ዉሳኔ ላይ መድረስ ይቻል ይሆናል:: ስለሆነም ትብብሩ ዉስጥ ገብቶ የተሻለ ሥርዓት ለማምጣት እንደመታገል በአንቀፅ 39 ምክንያት ትብብሩን እንቃወማለን ማለት ምን የፖለቲካ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ እንደታሰበና እንዴትም ሊተረጎም እንደሚችል ግልፅ አይደለም::

## 3.2 AFD እና የኤርትራ ሚና

ከትብብሩ ምሥረታ ጀርባ የኤርትራ እጅ አለበት የሚለዉ ጉዳይ ትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲን ለመቃወም ሌላዉ በዋናነት የሚነሳ የተቃዉሞ ነጥብ ነዉ። እንደ ዋና የተቃዉሞ ነጥብ ሆኖ የሚቀርብበት ምክንያትም ትናንት የኢትዮጵያ አካል የነበረችዉ ኤርትራ ዛሬ መንግሥት በመሆኗ ጠንካራ ኢትዮጵያን ማየት አትፈልግምና የኢትዮጵያን መበታተን ትመኛለች የሚል ነዉ። ስጋቱ ተገቢ አይደለም ማለት የማይቻል ቢሆንም ከአገራችን የወደፊት ህልዉና አንፃር የኤርትራን ሚና በተመለከተ ከትብብሩ ኋላ የኤርትራ መንግሥት አለና አንደግፈዉም ከማለት ዉጭ መታየት ያለባቸዉ በርካታ ጉዳዮች ያሉ ይመስለናል። እነዚህን ጉዳዮች ትንሽ ዘርዘር አድርገን እንያቸዉ።

የኤርትራ መሪዎች የመገንጠል ትግል ሲያካሂዱ ዋና ስትራቴጂ አድርገዉ የነደፉት ኢትዮጵያ ዉስጥ እየተካሄዱ ያሉ ሌሎች የብሔር ብሔረሰብ ቅሬታዎችና ጥያቄዎች ወደ መገንጠል ጥያቄ እንዲያድጉ፣ ሰላማዊ ንቅናቄዎች ደግሞ ጦርነት እንዲጀምሩ፣ የተጀመሩ ጦርነቶች ካሉ እንዲባባሱና የኢትዮጵያ መንግሥት ዙሪያዉን እንዲወጠር ማድረግን እንደሆነ አያጠያይቅም። ይህ ተቃዋሚዎችን የማጠናከር ጉዳይ ደግሞ ማንም ጠላት ተቀናቃኙን አገር ለመጉዳት የሚጠቀምበት ስልት ነዉ። የኤርትራ መሪዎች ከተገነጠሉም በኋላ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር በመሆኗ አንድ ቀን ትወረናለች፣ ትዉጠናለች የሚል ብሔራዊ ስጋት ይኖርባቸዉ ይሆናል። እኛንም ሁል ጊዜ የባሕር በር የማጣት ጉዳይ ጉዳይ እንደሚከነክነን ያያሉ፣ ይሰማሉና ስጋታቸዉ መሠረተ ቢስ ነዉ ማለት አይቻልም። ስለዚህ አንድ ቀን እንዳንወርራቸዉ ከቻሉ አገሪቱ እንድትበታተን፣ ካልቻሉም ሁልጊዜ በእርስ በርስ ጦርነት እንድትጠመድ አይፈልጉም አይባልም። ይህም ቢሆን ማንም ብልጥ ጠላት የሚያስበዉና የሚያደርገዉ ነዉ።

ኤርትራ ብቻ ሳትሆን ግብፅም በዓባይ ዉሃ ምክንያት የኛን መበታተንና መበጣበጥ ትፈልጋለች። ለዚህም ሌት ተቀን ትሠራለች። ይህ ለራስ ጥቅም ሌላዉን አገር በልዩ ልዩ መንገዶች መጉዳት ትናንትም የነበረ፣ ዛሬም ያለና ለወደፊቱም የሚኖር ነዉ።

እኛም እንዲሁ አገር ነን። ቢያንስ ከኤርትራ የበለጠ ሀብትና ኃይል አለን። ብልሆች ከሆንን አንድ አገር እርስ በርስ ሊያበጣብጠን ሲያስብ ወይም ሲነሣ ቀዳሚዉ ጥያቄያችን «እርስ በርስ ሊያበጣብጠን ነዉ» የሚለዉ ሳይሆን «መግቢያ ቀዳዳ አለዉ ወይ? ካለዉስ እንዴት እንዝጋዉ?» የሚል መሆን አለበት። ቀዳዳዉን የምንዘጋዉ በመካከላችን ከብሔር፣ ከሃይማኖት፣ ከቋንቋ፣ ከባህል፣ ከኢኮኖሚ፣ ወዘተ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን

ወይም ሌሎች ያልተፈቱ ወሳኝ ጥያቄዎችን በመፍታት ነዉ። ግትር አቋም ይዘን እነዚህን ቀዳዳዎች መዝጋት ካቃተን ማንም አገር ወይም የቅርብም ሆነ የሩቅ ጠላት በቀላሉ ያጠቃናል፣ ይበትነናል። ባልና ሚስት ሲጋጩ እንኳ በባህላችን የአስታራቂ ሽማግሌዎች ዋናዉ ምክር «በመሃላችሁ ንፋስ አይግባ» የሚል ነዉ። ነፋስ የሚገባበት ቀዳዳ የሚፈጠረዉ ደግሞ እርስ በርስ ሲጋጩና ትንሹን ግጭትም መፍታት ሲያቅታቸዉ ነዉ። በ«ነፋስ» የተሰየመዉም የጎረቤት ወይም የሩቅ/የቅርብ ጠላትና ምቀኛ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ሁልጊዜ እገሌ የሚባለዉ አገር የዉስጥ ችግሮቻችንን ተጠቅሞ ሊበትነን ነዉ ብለን እንዳንሰጋ ዋናዉ መፍትሔ መሆን ያለበት ቤታችንን ፈትሸን ቀዳዳ ካየን መዝጋት ነዉ።

የኤርትራ የቅድመ-ነፃነትና ድህረ-ነፃነት ፖሊሲ ምንም ይሁን ምንም ከ1990-92 ከሕወሐት መራሹ የኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ዘግናኝ ጦርነት ተዋግቷል። ተሸንፏልም። ሕወሐትም በዚህ ጦርነት ሰበብ በሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወጣቶችን አስጨፍጭፏል። ከዚያም በኋላ ጉዳዩ ለዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሕወሐት ቢሸነፍም ፍርዱ አልተፈፀመም። ስለዚህ የኤርትራ መንግሥት በሕወሐት ላይ ያለበት ጥላቻ ይህ ነዉ አይባልም። የኤርትራ መሪዎች ከማንኛዉም የአገራችን ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች ዉስጥ ሕወሐትን የሚጠሉትን ያህል ሌላ የሚጠሉት አለ ለማለት ይከብዳል። ይህንን ቡድን በተቻላቸዉ መንገድ ሁሉ ማጥቃትና መበቀል እንደሚፈልጉም አያጠራጥርም። ማንኛዉም አገር በአሁኑ ዘመን ጠላቴ ነዉ የሚለዉን ሌላ አገር የሚያጠቃበት ዋና መንገድ ደግሞ አማፂዎችን መርዳት ወይም መፍጠር ነዉ። ይህንን ስልት ደግሞ ሕወሐትም ይጠቀምበታል። ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚኖሩና ሕወሐት ትጥቅና ስንቅ የሚሰጣቸዉ የኤርትራ ተቃዋሚ ቡድኖች በርካታ ናቸዉ። በተጨማሪም ሕወሐት ላለፉት 15 ዓመታት በርካታ የሶማሌ የጦር አበጋዞችን ሲቀልብ ኖሯል። በዚህም እጅግ ብዙ የሀገር ሃብት አዉድሟል። ተቃዋሚዎችን ከመርዳት አልፎም የራሱን ወታደሮች ሶማሊያ ሉዓላዊ ግዛት ዉስጥ በማስገባት የፈለገዉን ሁሉ እያረገ ነዉ። በአጠቃላይ ሶማሊያ እንደአገር ተመልሳ እንዳታንሰራራ ዋናዉ እንቅፋት ሕወሐት ሆኖ ኖሯል። አሁንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ዉጭ ምን እየሠራ እንደሆነ እያየነዉ ነዉ።

የኤርትራም መንግሥት እያደረገ ያለዉ ይህንኑ ነዉ። የሕወሐትን መንግሥት ተቃዋሚዎች መርዳት ከቻለም ማስታጠቅ። በዚህም መሠረት የኤርትራ መንግሥት እንደ ኦነግና ኦብነግ ካሉ የነፃነት ግንባሮች ጋር የቆየ ግንኙነት ይኖረዉ ይሆናል። ከቅንጅት ጋር ግን የዚህ ዓይነት ግንኙነት አለዉ ማለት ያስቸግራል። በአጠቃላይ ግን የኤርትራ መንግሥት የትኞቹንም የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችን ሲረዳ ዋና ግቡ ብሔራዊ

ጥቅሙን ማስከበርና ሕወሐትን ማዳከም ወይም መጣል ነዉ። ሕወሐት መራሹ መንግሥት በዉስጥ ችግርና ቅራኔዎች ከተጠመደ ለኤርትራ መንግሥት ስጋት አይሆንም ብሎ ያስባል። በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚ ቡድኖች ሁሉ በተቻላቸዉ መንገድ ሁሉ ዕርዳታ ከሚሰጣቸዉ አገር ጋር ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር ይሞክራሉ። ዋና ዓላማቸዉም የሚፈልጉትን ዕርዳታ አግኝተዉ ጠላታቸዉ የሆነዉን መንግሥት መዋጋት እንጂ የሚረዳቸዉን አገር ፖሊሲ በቀጥታ ማስፈፀም አይደለም። የሌላዉን አገር ፖሊሲ የሚያስፈፅም ቡድን ቅጥረኛ ይባል እንደሆነ እንጂ ተቃዋሚ አማፂ ሊባል አይችልም።

እንዳሁኑ ባለ ዘመን የትጥቅ ትግል ማካሄድ ከባድ ነዉ። በተለይም ለአስፈላጊ ነገሮች አቅርቦት መሸጋገሪያ የሚሆን የጎረቤት አገር ማግኘት ወሳኝ ነዉ። በዚህ ጊዜ ማንም ቡድን የሆዱን በሆዱ አድርጎ ከማንም አገር ዕርዳታ ይቀበላል። በተለይ ከጎረቤት አገር። የኛ አገር ተቃዋሚ ድርጅቶችም ይህን ቢያደርጉ አዲስ ነገር አይደለም። አንድን ሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት ለመጣል የሚታገል አማፂ ቡድን ዕርዳታን ከሰይጣን ነዉ ወይስ ከመልዓክ ነዉ ብሎ አያማርጥም። ተቃዋሚዉ ድል ካረገ በኋላ ግን የሚያስቀድመዉ የአገሩን ብሔራዊ ጥቅም እንጂ በጦርነት/በትግል ጊዜ የረዳዉን የጎረቤት አገር ጥቅም አይደለም።

እዉነታዉ ይህ ሆኖ ሳለ የAFD ተቃዋሚዎች የኤርትራ መንግሥት በብልጠት ከእኛ ስለሚበልጥ የሕወሐት መንግሥት ተቃዋሚዎች የሆኑ ድርጅቶቻችንን ያታልላቸዋል የሚል ስጋት ካላቸዉ ራስን ዝቅ አድርጎ የማየት ችግር ይመስለናል። የኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች ብልጥ ሆነዉ በኤርትራ መንግሥትና በሕወሐት መካከል ያለዉን ቅራኔ ተጠቅመዉ (exploit አድርገዉ) አረመኔዉን የሕወሐት ገዢ ቡድን ሊያሰወግዱልን ቢሠሩ ብልህነት ነዉ እንጂ ሞኝነት አይደለም። የፖለቲካ ዓለም ደግሞ የብልጠትና ለራስ የሚበጅን መንገድ (advantage) ብቻ የማየት ዓለም ነዉ። ፖለቲካ ማለት ሥነ-መለኮት (theology) አይደለም።

በሌላ በኩል ኤርትራ የኛን ድርጅቶች ስትረዳ ዓላማዋ ኢትዮጵያን ለመበተን ከሆነ ለዚህ የሚተባበራት ከሕወሐት የበለጠ ታማኝ ሎሌ እና መልዕክተኛ እንደማታገኝ ታዉቃለች። በየትኛዉም መሥፈርት ሕወሐትን የመሰለ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በመጥላት በአንድነቷ ላይ ያነጣጠረ ቡድን ሊፈጠር አይችልም። ሕወሐትን የፈጠረዉ፣ ያሳደገዉ፣ ያስታጠቀዉና ለዛሬዉ ሥልጣን ያበቃዉ ደግሞ የአሁኑ የኤርትራ መንግሥት የሆነዉ ቡድን ነዉ። ሕወሐት ታዲያ የራሱ ጥቅም ሲመጣ ፈጣሪዉ የሆነዉን የኤርትራን

ቡድን ከድቷል፡፡ ኤርትራ አሁን ሌሎቹን የምታስጠልለዉ ለዚሁ ዓላማ ከሆነ (እዉነትም ቅንጅትና ሌሎች የሕወሐት ተቃዋሚዎች ኢትዮጵያን ይበትኑልኛል ብላ ከሆነ) የኤርትራ መሪዎች ሞኝ ናቸዉ ማለት ነዉ፡፡ ግን ሞኝ አይደሉም፡፡ የዘለቄታ ጥቅማቸዉን ያዉቃሉ፡፡ ብዙ የኤርትራ ፖለቲከኞች ሲጽፉ አሁን ካሉት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ቡደኖች ሁሉ ለዘለቄታ ጥቅማችን ሕወሐት ይሻለናል፣ ምክንያቱም ሕወሐት በኤርትራ ሉዓላዊነት ላይ የማያወላዉል ድጋፍ አለዉ ይላሉ፡፡ ሌሎቹ ግን ልባዊ ድጋፍ የላቸዉም የሚል ነዉ ትንተናቸዉ፡፡ ሕወሐት ራሱም ቢሆን በፕሮፓጋንዳዉ የሚደጋግመዉ ይህንኑ ነዉ፡፡ ቁንጮዉ ሰዉዬ ራሳቸዉም በቅርቡ ከ«ፓርላማ አባላት» ለቀረቡ ጥያቄዎች የሠጡት መልስ ተብሎ በመገናኛ ብዙሃን በተላለፈዉ ማብራሪያቸዉ ለኤርትራ ሉዓላዊነት ከኢሕአዴግ የሚቀርብ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይል/ቡድን እንደሌለና እንደቅንጅትና የአርበኞች ግንባር የመሣሰሉት የኤርትራን ሉዓላዊነት የማይቀበሉ ቡድኖች አባል የሆኑበትን AFDን የኤርትራ መንግሥት መርዳት እንዳልነበረበት በቁጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ እንደመሪያቸዉ ሁሉ ሌሎችም የሕወሐት ካድሬዎችና የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች ዘወትር የሚያነሱት ጥያቄ «እኛ የኤርትራን ነፃነት ከልብ የምንደግፍ ሆነን ሣለ እንዴት ሌሎች እኛን የሚቃወሙ ቡድኖችን ኤርትራ ትረዳለች?» የሚል ነዉ፡፡

ትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲን ተቃወምን የሚሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የኤርትራን ድጋፍ ይቃወሙ እንጂ በሕወሐት የግፍ አገዛዝ ሥር የመከራ ሕይወት እየኖረ ያለዉ የአብዛኛዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኞት ግን «ተቃዋሚ ድርጅቶች እንኳን ከኤርትራ ጋር ቢቻል ከሰይጣንም ጋር ቢሆን ተባብረዉ ከዚህ ልጆቻችንን በመጫወቻ ሜዳቸዉ እያደነ ከሚያርድ ጭራቅ በገላገሉን» የሚል ነዉ፡፡ የእኛ ተቃዋሚዎች ትልቁ ድክመት እንዲያዉም የዚህ ዓይነት ዕድሎችን የበለጠ ተጠቅመዉ ከሌሎች መንግሥታት ድጋፍ በመጠየቅ ትግሉን ለማጠናከር የሚያስችል የብልጠት ሥራ በበቂ ሁኔታ አለመሥራታቸዉ ነዉና ለዚህ ድክመታቸዉ በደጋፊዎቻቸዉ በጣም መወቀስ ነበረባቸዉ፡፡

ይህን ሁሉ ሀተታ ለመደርደር የተገደድነዉ AFDን በሚቃወሙ ወገኖች በኩል «ለትብብሩ ምሥረታ የኤርትራ መንግሥት እጅ አለበት» የሚሉትን የተቃዉሞ ሀሳብ እዉነተኛ ወሬ እንደሆነ እሳቤ በመዉሰድ ነዉ፡፡ ነገር ግን ለትብብሩ ምሥረታ ኤርትራ ስለማገዟ ምንም ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ትብብሩን የሚቃወሙ ወገኖች ኤርትራን አስመልክተዉ እንደሚያነሱት ስጋት ከሆነ፣ ለኤርትራ የዘለቄታ ጥቅም

የሚበጀዉ እንዲያዉም የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች መቀራረብ ሳይሆን መጋጨታቸዉ ነዉ።

በሌላ በኩል መታወቅ ያለበት ደግሞ የ"AFD"ን ዓይነት መድረክ ለመፍጠር ሲሞከር የነበረዉ ከበርካታ ዓመታት በፊት ጀምሮ የመሆኑ እዉነታ ነዉ። እንዲያዉም ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩት አሁን ትብብሩን ለመቃወም ግንባር ቀደም የሆኑት ቡድኖችና ግለሰቦች መሆናቸዉን ብዙዎቻችን በሚገባ እናስታዉሳለን።

በአጠቃላይ ኤርትራ ስላለችበት (ስለደገፈችዉ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር እንደጥሩ ተስፋ አድርጎ ያየዉንና በሙሉ ልብ የተቀበለዉን ትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲን አንቀበልም ማለት አንድም የሌላ ድብቅ ዓላማ ሽፋን ነዉ ወይም የፖለቲካ ልምድ ያለመኖር ነዉ።

AFDን የፈጠረችዉ ኤርትራ ነች ብሎ ማሰብ በሌላ መልኩ ቅንጅትንም፣ ኦነግንም ሌሎቹንም ድርጅቶች የፈጠረችዉ ኤርትራ ነች ብሎ እንደማሰብ ነዉ። ነገር ግን ኦነግ ከሰላሣ ዓመታት በላይ የቆየ እንቅስቃሴን የሚወክል ሲሆን ቅንጅትም ኢትዮጵያ ዉስጥ በህጋዊ መንገድ የተቋቋመና እጅግ በጣም ብዙ ኢትዮጵያዉያን የሚደግፉት ፓርቲ ነዉ። በሌላ በኩልም ኤርትራ የእኛን ተቃዋሚዎች የምትፈጥር ከሆነ የገዢዉ ቡድን ተቃዋሚ የሆኑ ድርጅቶች እንዲፈጠሩና ትግል እንዲያደርጉ የሚያስገድድ የፖለቲካ ሁኔታ በኢትዮጵያ አልነበረም ወይም የለም ማለት ነዉ። ይህም ማለት ሰዎችን ለትግል የሚያነሣሣ/የሚገፋፋ ዘግናኝ የሆነ የሰብዓዊ መብት ረገጣና አፈና የለም ብሎ እንደመካድ ነዉ።

ሁላችንም እንደምናዉቀዉ አትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ጭቆና፣ አፈናና የመብት ረገጣ ለተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች መፈጠር ምክንያት ሆኗል። በሕዝብ ላይ የሚደርሱ በደሎችን የሚታገሉ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች እስካሉ ድረስ ደግሞ የአባላትና የደጋፊዎች መኖር የግድ ነዉ። እነዚህ አባላትና ደጋፊዎች የየፓርቲዎቹ/ድርጅቶቹ መሪዎች ማናቸዉንም ዉጤታማ የሚያደርጉ አመቺ የትግል ስልቶችን በመጠቀም ለድል እንዲያበቋቸዉ አይፈልጉም ማለት አይቻልም። ለምሳሌ ቅንጅትን የምንደግፍ ሁሉ ለቅንጅት ድጋፍ እናደርጋለን ካልን ፓርቲዉ የተለያዩ ስልቶችን ቀይሶ ለድል እንዲያበቃን እንፈልጋለን ማለታችን ነዉ። አንድ ፓርቲ ዉጤት ሊያስገኝ የሚችል ታክቲክና ስትራቴጂ ነድፎ ለድል ካላበቃንና አሁን የተጠማነዉን ዲሞክራሲ አስገኝቶ ሕዝባችንን ከሕወሐት ምርኮኛነት መሪዎቻችንንና

በግፍ የታሠሩ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችንም ነፃ ካላወጣ እንኳን የፖለቲካ ፓርቲ የመንደር ዕድርም ሊባል አይችልም:: የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን ከሚያስፈልጓቸዉ ስልቶች ዋነኛዉ ደግሞ በመካከላቸዉ ህብረት/ትብብር በመፍጠርና ትግሉን በተለያየ መንገድ ሊረዱ ከሚችሉ መንግሥታት ሊገኙ የሚችሉ ዕርዳታዎችን ሁሉ በመጠቀም የጋራ ጠላትን መዋጋትና ድል ማድረግ ነዉ:: ከአሁኑ ጠንካራ ትብብር መመሥረት ደግሞ ከማይቀረዉ ድል በኋላ አላስፈላጊ የርስ በርስ ግጭቶችን ለማስወገድ ከአሁኑ ጠንካራ መሠረት መጣልም ጭምር ነዉ እንላለን:: የትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲ መንፈስና አካሄድም ይህ ይመስለናል::

እንዲሁ በደፈናዉ «የኤርትራን መንግሥት ስለምንጠላ ኤርትራ የምትባል አገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አለችበት» የተባለን ማንኛዉንም ነገር አንቀበልም የምንል ከሆነ ሥራችን ዉጤት ሊያስገኝ የሚችል የፖለቲካ ሥራ ሳይሆን ተራ የጊዜ ማሳለፊያ (hobby) ሆነ ማለት ነዉ:: የፖለቲካንና ዓለም አቀፍ ግንኙነትን መርሆዎች ጠንቅቀዉ የሚያዉቁ ጠበብቶች እንደሚሉት በፖለቲካና በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ሥራ ዉስጥ ዘላቂ ፍላጎት ወይም ጥቅም እንጂ ዘላቂ ጠላት የሚባል ነገር የለም (in politics and international relations, there is no permanent enemy but permanent interest):: የዘመኑ ጨወታ ደግሞ መሆን ያለበት ያሰቡትን ለማግኘት ወይም ከሚፈለገዉ ግብ ለመድረስ በተቻለዉ መንገድ ሁሉ ጠላትን እያሳነሱ ወዳጅን ማብዛት ነዉ::

ስለሆነም አገርንና ሕዝብን ነፃ ለማዉጣት የቤተሰብ ሕይወታቸዉን፣ ምቾታቸዉንና ሌሎችንም የግል ጥቅሞቻቸዉን ወደጎን በመተዉ ሕይወታቸዉን ጭምር ላመኑበት ክቡር ዓላማ ለመስጠት ወስነዉ ወደትግል የገቡ ቆራጥ የድርጅት መሪዎች ከኤርትራ መንግሥት ለሚያገኙት ጊዜያዊ ዕርዳታና ጥቅም ሲሉ ምትክ የማይገኝለት ሕይወታቸዉን ጭምር አሳልፈዉ ሊሰጡ ቆርጠዉ የገቡበትን ዓላማ ይስታሉ ብለዉ የኤርትራን ድጋፍ (በእዉነትም ድጋፉ ካለ) እንደ አንድ የትብብሩ መቃወሚያ ነጥብ የሚያቀርቡ ወገኖች ራሳቸዉ ቆመንለታል ለሚሉት ዓላማ ምን ያህል ታማኝ እንደሆኑ እንድንጠይቃቸዉ ሳያደርጉን አልቀሩም:: እነዚህን የAFDን ተቃዋሚዎች በፖለቲካ ጥገኝነት የተቀበሏቸዉና የሚረዷቸዉ የአዉሮፓና የሌሎች አገሮች መንግሥታት ህሊናቸዉ ከሚቀበለዉ ዉጭ እንደፈለጉ ያሽከረክሯቸዋል ማለት ነዉ? ወንድም የሆነዉ የኤርትራ ሕዝብና አሁን ሥልጣን ላይ ያለዉ የኤርትራ መንግሥት እንደጥሩ ጎረቤት ብቻ ሳይሆን ሕወሐት መራሹን መንግሥት በራሱ ምክንያቶች እንደሚቃወም የጎረቤት አገር የተለያዩ የሕወሐት ተቃዋሚ ድርጅቶችን የማቀራረብ ሚና ተጫዉቶ ከሆነስ ክፋቱ ምኑ ላይ ነዉ? የዚህ ጽሑፍ አቅራቢዎች ሌላዉን ሁሉ ትተን ትብብሩን

ለመመሥረት በወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ብቻ እንኳ የምናከብራቸዉና በጣም የምናደንቃቸዉ የAFD መሥራች ድርጅቶች መሪዎች እንደ ህፃን በጥቃቅን ጊዚያዊ ጥቅሞች ይታለላሉ፣ በዚህም የአገራቸዉንና የቆሙለትን ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም አሳልፈዉ ለኤርትራ መንግሥት ይሰጣሉ ብለን በፍፁም አናስብም::

## መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅን፣ ደግ፣ አርቆ አሳቢ፣ ጀግናና ለየትኛዉም መከራ የማይበገር መንፈስ ጠንካራ ሕዝብ የመሆኑን ያህል የሚፈልገዉን ዓይነት አመራር ለማግኘት ግን የታደለ ሕዝብ አይደለም:: የጨቋኝ ገዢዎቻችን ተቃዋሚዎች ነን የሚሉ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችም የተለያዩ ማራኪ ስሞችን ይዘዉ ቢነሱም ቆመንለታል ከሚሉት ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም ዉጭ ለራሳቸዉ ታዋቂነት፣ የግል ጥቅምና ዝና፣ ብሎም የስልጣን ጉጉት ሲሉ በየጥቃቅን ምክንያቶቹ መጠላለፍን ዋና ተግባራቸዉ ያደረጉ ነበሩ:: ይህም የፖለቲካ ትግላችን ባለበት እንዲረግጥ ምክንያት ሆኗል:: AFDን የመሠረቱት ድርጅቶች ግን ከምንም በላይ ለዚህ ሕዝብ ሲሉ የግል ፍላጎታቸዉን ሁሉ ወደጎን በማድረግና ካለፉት ስህተቶቻቸዉ በመማር የትብብሩን እርምጃዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚፈልገዉ አቅጣጫ ያደርጋሉ ብለን እንገምታለን::

ወደድንም ጠላንም ድህረ-ሕወሐት የነበረዉ አካሄዳችን ሁሉ (በግል ግንኙነቶቻችን ሳይቀር) የብሔር ብሔረሰብ ጆርባችንን እንድንጠያየቅ ወደሚያስገድደን ሁኔታ ያዘነበለ ነበር:: የAFD መመሥረት አንዳንድ መጠነኛ ለዉጦችን እንዳመጣ መካድ ባይቻልም አሁንም ቢሆን ከዚያ አዝማሚያ ሙሉ በሙሉ እንድንወጣ የሚያደርጉን ፍንጮች ጎልተዉ አልታዩንም:: በሕወሐት ሥር የኖርንበት ጊዜ አጭር ባለመሆኑ ያዳበርነዉ ብሔር ብሔረሰብን መሠረት ያደረገ ልምድ ቀላል የሚባል አይደለምና:: ሕዝባችንን ከዚህ ከፋፋይ ሁኔታ ለማዉጣትና በአንድ ዓላማ ሥር ለማሰለፍ በህብረ ብሔርነትና በብሔር ብሔረሰብ ድርጅትነት ጎራ ተለይተዉ የሚታወቁ ድርጅቶች በሙሉና፣ ሰፊ ሕዝባዊ መሠረትና ድጋፍ ያላቸዉ ድርጅቶች ደግሞ በተለይ ብዙ መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: በዚህ ረገድ ቅንጅትና ኦነግ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት አለባቸዉ ለማለት እንደፍራለን:: ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ማንቀሳቀስ የሚችሉት የሕዝብ ቁጥር እጅግ ብዙ፣ የሚሸፍኗቸዉ የአገራችን ክልሎችም በጣም ሰፊ መሆኑን በተግባር ያሳዩ ድርጅቶች ናቸዉና:: ኦነግ በ1992 ምርጫ በመላዉ ኦሮሚያ ያሳየዉን ሰፊ የሕዝብ ድጋፍና ተቀባይነት ቅንጅት በ2005ቱ ምርጫ በተጠናከረ ሁኔታ አሳይቷል:: ለዚህም ነዉ የእነዚህ ሁለት ድርጅቶች ከትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲ መሥራቾች መካከል መሆን አገር ዉስጥ የሚኖረዉንም ሆነ ከአገር ዉጭ ያለዉን አብዛኛዉን

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከልብ ያስደሰተዉ። የዚያኑ ያህል ደግሞ የእነዚህ ሁለት ድርጅቶች ሌሎችንም ተቃዋሚዎች ባካተተ ትብብር ዉስጥ መግባት ብቻ ሳይሆን የጎላ ተሳትፎ ማድረግ ቁንጮዉን ሰዉዬ ጨምሮ ሁሉንም የገዢዉን ቡድን አባላትና የሥርዓቱን ተጠቃሚዎች እንቅልፍ የነሳቸዉ።

ስለሆነም ትብብሩ መመሥረቱ ብቻ በራሱ እንኳ እጅግ አበረታችና ተስፋ ሰጪ ጅምር ነዉ። ይሁን እንጂ ለበለጠ ዉጤት እስካሁን ካየነዉ አልፎ መሄድ ተገቢ ይመስለናል። ለዚህ ደግሞ የሚከተሉትን እርምጃዎች መዉሰድ አስፈላጊ ነዉ ብለን እናስባለን፡-

1. በመሠረቱ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጎልቶ ይሰማ የነበረዉ የኦነግም ሆነ የሌሎች የነፃነት ግንባሮች «የመገንጠል» ጥያቄ ለኢትዮጵያ አንድነት አደጋ የሚሆነዉን ያህል «የአገር አንድነት» በሚል ስም የምናሰማዉ ባዶ መፈክርም ለአገራችን አንድነትና ህልዉና የሚበጅ አካሄድ አይደለም። በሌላ አባባል ከሌላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ መገንጠልን እንደ መፍትሔ የሚወስደዉ የነፃነት ግንባሮች አካሄድ ለአገራችን ህልዉና እንደማይበጅ ሁሉ የህዝቦችን የዲሞክራሲ፣ የነፃነትና የእኩልነት መብት ከግምት ያላስገባ አንድነትም ለአብሮነታችን እጅግ አደገኛ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በመሆኑም እስከአሁን ከተፈጠረዉ የጋራ ግንዛቤና ከተገኘዉ የሕዝብ ድጋፍ አልፎ ለመሄድ ህብረ ብሔር የሆኑትም ሆኑ የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶች አቋማችን ናቸዉ ብለዉ ከያዟቸዉ አካሄዶች አልፈዉ መሄድ ያለባቸዉ ይመስለናል። ስለሆነም፡-

> ሀ. «በአደረጃጀታችን ህብረ ብሔርና በአቋማችንም የአንድነት ኃይሎች ነን» የሚሉት ፓርቲዎች ኢትዮጵያ የሕዝቦችን መብት ክፉኛ በሚረግጡ የአገዛዝ ሥርዓቶች ሥር እንደነበረችና የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች በገዛ አገራቸዉ እንደሁለተኛ ዜጋ ይታዩ የነበረበት ሁኔታ እንደነበር ይህም ለነፃነት ግንባሮች መፈጠር ምክንያት እንደሆነ በማመን ይህን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ዜግነት ሥዕል ለመቀየር በቁርጠኝነት መቆማቸዉን በተጨባጭ ማሣየት ይኖርባቸዋል።
>
> ለ. ኦነግና ሌሎቹ የነፃነት ግንባሮችም ፍትሃዊ ጥያቄዎቻቸዉ አጥጋቢ መልስ እስካገኙ ድረስ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚሠሩ መሆናቸዉን በግለሰብ የአመራር አባላት በሚሰጡ መግላጫዎች ብቻ ሳይሆን የየግንባሮቹ አቋም መሆኑን በግልፅ በሚያሳይና ምንም በማያሻማ መንገድ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። በተለይም ኦነግ ብዙ ቁጥር ካለዉና ሰፊ መሬትን ከሚሸፍነዉ የአገሪቱ ሕዝብ አብራክ እንደወጣ ድርጅትና በሁሉም መንገድ ለኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት መሆኑ ለማያጠያይቀዉ የኦሮሞ ሕዝብ ቆሜያለሁ እንደሚል ድርጅት የህዝቡ መብት በፌዴራላዊና

በእዉነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዉስጥ እስከተከበረ ድረስ ለኢትዮጵያ ህልዉና ግንባር ቀደም ሚና የመጫወት ታሪካዊ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ያለማወላወል መቀበልና ይህንኑም በተግባራዊ እርምጃዎቹ ማሣየት መቻል አለበት።

የዚህ ዓይነት ግልፅ አቀራረብ የፅንፈኝነት አቋም ያላቸዉን የየድርጅቶቹን አባላትና ደጋፊዎች ለጊዜዉ እንደሚያስቆጣና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ድርጅቶቹን ሊጎዳ እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ይሁን እንጂ ከምንም በላይ የሁላችንም የጋራ አገር ህልዉና ጉዳይ በሚገባ በታሰበበት መንገድ ከተያዘና መሠራት የሚገባቸዉ የፖለቲካ ሥራዎች የእያንዳንዱን ዜጋ የልብ ትርታ ባዳመጠ መንገድ የሚሠሩ ከሆነ ዉጤታማ መሆን ስለሚመጣ ለጊዜያዊ ተቃዉሞዎች ቦታ መስጠት ተገቢ አይሆንም። ቅንነትና ቆራጥነት በተመላበት መንገድ ተንቀሳቅሶ ወደፊት መራመድና አርኪ ዉጤቶችን ማስመዝገብ ከተቻለ ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍ ማግኘት ከባድ አይሆንምና። ከዚህ በላይ በ«ሀ» እና በ«ለ» የተገለፁትን እርምጃዎች መዉሰድ ከተቻለ ሕወሐትም ሆነ ሌሎች የትብብሩ ተቃዋሚ ወገኖች ትብብር መሥራች ድርጅቶቹንም ሆነ ሕዝባችንን ሊከፋፍሉ ከሚችሉባቸዉ ቀዳዳዎች መካከል ዋናዉ ተደፈነ ማለት ነዉና በሚገባ ሊታሰብበት ይገባል።

2. ባለፉት አሥራስድስት ዓመታት የአገራችን ፖለቲካ ባለበት ከመርገጥ ወይም የኋሊዮሽ ገዞ ከማድረግ ወጥቶ አንድ እርምጃም ቢሆን ወደፊት ተራምዷል ሊያሰኘን የሚችል አንድ ተጨባጭ ዉጤት ቢኖር የAFD ምሥረታ ነዉ። AFD ፖለቲከኞቻችንና የፖለቲካ ድርጅቶቻችን ብልህነትን፣ አርቆ አስተዋይነትንና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ተከትሎ አመቺ ስልት የመቀየስን ብቃት ያሳዩበት ትልቅ እርምጃ ነዉ። የሚያሳዝነዉ ግን ከምንም በላይ የአገራችንን መሠረታዊ ችግሮች በጥልቀት ገምግመዉ AFDን ለመደገፍ ግንባር ቀደም ይሆናሉ ተብለዉ የሚጠበቁ ድርጅቶችና ፖለቲከኞች ዋና ተቃዋሚዎች ከመሆንም አልፈዉ በጣም ተራ የሆኑ ምክንያቶችን በመደርደር ለአገራቸዉ በጎዉን ሁሉ የሚመኙ የተወሰኑ ኢትዮጵያዉያንን ብዥታ ዉስጥ ማስገባታቸዉ ነዉ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን አገር ዉስጥም ሆነ ዉጭ ያለዉ የአገራችን የወቅቱ ፖለቲካ ዉስብስብነት የገባዉ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ AFDን ከልብ እንደሚደግፍ በግልፅ ታይቷል።

በመሆኑም ይህን የሕዝብ ድጋፍ በመጠቀም AFDን ከፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር ወደ ኢትዮጵያ ህዝቦች ትብብር ማሸጋገር ተገቢ የሚሆንበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

እንደሚታወቀዉ አብዛኛዉ ሕዝባችን AFDን የሚደግፍበት ዋናዉ ምክንያት የዚህ ዓይነቱ ትብብር ከምንም በላይ ለአገራችን ዘላቂ አንድነት ብቸኛዉ መንገድ በመሆኑ ነዉ፡፡ ለምሳሌም፡- የገዢዉ ቡድን እጅ አለበት የሚባለዉንና በሃይማኖት ሰበብ በቅርቡ በጂማ አካባቢ የተከሰተዉን ዓይነትና ሌሎችንም ሕዝባችንን እርስ በርስ ለማጋጨት የሚደረጉ ሙከራዎችን ማክሸፍ የሚቻለዉ የAFD ዓይነቱ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር ሲኖርና በዚህም ሰበብ ሕዝባችን ተቀራርቦ ሲወያይና ሲመካከር እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ ስለሆነም የአገራችን የወደፊት ህልዉና የሚያሳስበን ኢትዮጵያዉያን ሁሉ AFDን የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር ከመሆን በላቀ ደረጃ ወደኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘላቂ የትብብር መድረክነት ማስፋትና ማሸጋገር አለብን፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ለትብብሩ ያለንን ልባዊ ድጋፍ በየፓልቶክ ሩሞች ከመግለፅ፣ ልዩ ልዩ የድጋፍ ጽሑፎችን ከማቅረብና በየግል ግንኙነታችን ከመወያየት አልፈን ተጨባጭ ድጋፍ ማድረግ ወደሚያስችሉን እንቅስቃሴዎች መሄድ ተገቢ ይመስለናል፡፡ በዚህም መሠረት ትብብሩን ከልብ የሚደግፉ ኢትዮጵያዉያን በሚኖሩባቸዉ አገሮችና ከተሞች ሁሉ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ የፖለቲካ ድርጅት አባልነት/ደጋፊነት፣ የትዉልድ አካባቢ፣ ወዘተ ሳይለያዩን ተቀራርበን በመነጋገር በአንድ የጋራ ዓላማ ሥር ዉጤታማ ሥራዎችን መሥራት የሚያስችሉንን የAFD ድጋፍ ቡድኖችን ማቋቋምና በቡድኖቹም አማካይነት ተጨባጭ የድጋፍ እርምጃዎችን መዉሰድ መጀመር ወይም እንደየአገሩና አካባቢዉ አመቺ ናቸዉ የሚባሉ ሌሎች ተግባራዊ የድጋፍ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ መወሰድ ከሚገባቸዉ ወቅታዊ እርምጃዎች የመጀመሪያዎቹ ናቸዉ፡፡

============//============